# የልማት ስንቅና ትጥቅ መስቀል!!

ስሜነህ

የ2004 ዓ.ም ማገባደጃ የሆኑት ሦስት ወራቶች በኢትዮጵያ ምድር ጥሩ አልነበሩም ማለት ይቻላል፡፡ በተለይ የቀድሞው የኢህአዴግ ሊቀመንበር እና የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መታመምን ተከትሎ ሀገሪቱ በወሬና አሉባልታ የታጠነችባቸው ወራቶች ነበሩ፡፡ አቶ  መለስ ዜናዊና አመራራቸው በሚከተሉት የልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ስኬት ጥቅማችን ይቀርብናል ብለው የሚያስቡትና በውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን ያልተደሰቱት ምዕራባውያን በተለያዩ ተለጣፊ ስሞች ባቋቋሟቸው ድርጅቶች አማካይነት አገሪቱን አስመልክተው የሚሰጧቸው መግለጫዎችና የሚያወጧቸው ሪፖርቶች ፍፁም ተዓማኒ ያልሆኑና የማይጨበጡ ቢሆኑም፤ ግባቸውን ሥልጣን ባደረጉ ተቃዋሚዎችና ለሆዳቸው ባደሩ ፕሬሶች አማካይነት አጀንዳ በማራገብ ከመቼውም ጊዜ በተለየ መልኩ ሀገሪቱ በወሬና አሉባልታ ታምሳ ከርማለች፡፡

ከመለስ መታመም በኋላ ነፋሱ ጨመረ አልኩ እንጂ ነገርዬውና የትርምስ አጀንዳው መለቀቅ የጀመረው በጣም ቀደም ብሎ ወይም ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ መሆኑ ይታወቃል፡፡

መሽቶ በነጋ ቁጥር እነ ሂዩማን ራይትስ ዎችና ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ ኢትዮጵያን በመግለጫና ሪፖርት ያብጠለጥላሉ፡፡ እነ ቪ.ኦ.ኤና መሰል ድረ ገፆች ደግሞ ጉዳዩን ሰማይ በማስነካት ያውለበልባሉ፡፡ የሀገሬ ጋዜጠኞችና ፕሬሶች ደግሞ የእናታቸውን ጡት ለመንከስ ፋታ የላቸውም። የበለጠውኑ ከሂዩማን ራይትስ ዎችና ከነ ክራይስስ ግሩፕ በላይ ዓይናቸው ሥር ያሉ ጉዳዮችን ጭምር እንዳላየ ሆነው ያስጮሃሉ፡፡ ተቃዋሚው ደግሞ ጊዜ ሳይወስድ መግለጫ ይሰጣል፤ መግለጫውን ደግሞ ተመልሰው እነ ሂዩማን ራይትስ ዎች ትክክል ነው ሲሉ አድናቆት ይቸሩታል፡፡ የአመፃ ዱላ ቅብብሉም ይቀጥላል፡፡ ሕዝቡም ከሥራ ገበታው ላይ ሆኖ ይህንኑ የተንዛዛ ወሬ ለማኘክ ይገደዳል፡፡

መንግሥት እንደ መንግሥት የሕዝቡን ሠላምና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታውን ለመወጣት በህግና ህገ መንግሥቱ በሚፈቅደው መሠረት የሚያወጣቸው ህጎችና አፈፃፀሞችም እንደገና ለነ ሂዩማን ራይትስ ዎች አዲስ አጀንዳ ይሆኑና ሌላ እሣት ይለኮሳል፡፡ የፀረ ሽብርተኝነት ህጉንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የተመለከተውን አዋጅ ተከትሎ የሊዝ አዋጁና የግብር ሥርዓቱ፣ የዋልድባ ጉዳይና እነ አወልያ የዙቃላ ገዳም የእሣት ቃጠሎ ሳይቀሩ እንደ ሰብዓዊ መብት ረገጣ ተወስደው ብዙ ተብሎላቸዋል፡፡

ከዐረቡ ዓለም አብዮት ጋር ተያይዞም በሰፋፊ እርሻ ልማቶች ስም የትርምስ ሱባኤ ተገብቷል፡፡ ብቻ በየቀኑ የማይፈነቀል ድንጋይ ያልነበረ ሲሆን ሃይ ባይ የሀገር ሽማግሌዎችንና እውነታውን ተናጋሪ ሀገር ወዳድ ዜጎች ሳይቀሩ የእነዚህ ኃይሎች የስድብ ናዳ ተለቆባቸዋል፡፡

እያለ...እያለ ነገርዬው የመለስ መታመም ጋር ሲደርስ ደግሞ “እግዚአብሔር ይማርህ” የሚለው ባህላችን በሞተዋል ተተክቶ ይህች ሀገር አበቃላት የሚል ድቤ ተደብድቧል፡፡ አቶ መለስ ባረፉ እለት እና የሀዘን ሥነ ሥርዓቱ ላይም ተሰልቋል፡፡ ከዚያም ህገ መንግሥት እንደሌላት ሀገር ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ነጠላ ዜማ በአየር ላይ ውሏል፡፡ በቃ ተናጭተዋል፣ ኢህአዴግ እንደ ግንባር በቴስታ ተላትሟል የሚል ነጋሪትም ተጎስሟል፡፡ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ከተከናወነ በኋላም ቢሆን ማላዘኑ አልቆመም፡፡ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ላይ ብዙ ዶሴ ተጽፏል፤ መጽሐፍ ተገልጧል፤ አይችሉም ተሰብኳል፡፡ እምነታቸው ተተንትኗል፤ ህገ መንግሥት ይግዛን ሲሉ የከረሙትና ህግና ህገ ወጥነትን የሚያጣቅሱ የሚባሉት እኩዮች በእርግጥም ኢትዮጵያ የሁሉም ኃይማኖትና ብሄሮች መሆኗን ያረጋገጠችበት የሥልጣን ሽግግር ላይ በማላገጥ የእፉኝት ልጆች ስለመሆናቸው ራሳቸው ምስክር ሆነዋል፡፡

ኢህአዴግና ኢህአዴግ መራሹ መንግሥት ግን የመለስ ሞት የበለጠ ጉልበትና ኃይል ሆኗቸው በአስተማማኝ ደረጃና ቁርጠኝነት ሥራቸውን እያከናወኑ ነው፡፡ የከተሜው ወሬና የወሬ ጠንሳሾቹ ተግባር በእርግጥም በከተማ አካባቢ ለሚኖረው ዜጋ ግራ የሚያጋባና ተነሳሽነትን የሚገድብ ከወሬ ጋር ብቻ ለመጋባት በር የሚከፍትና ከሥራ የሚነጥል ከመሆኑም በላይ ሲበዛ ማር ይመራል እንዲሉ ዳግም ምንችክ ሲል የበለጠ ወደ ላይ ያስብላል።

እድሜ ለመስቀል፡፡ መስቀልና ክርስትና፣ መስቀልና ቱሪዝም፣ መስቀልና ፌስቲቫሉ ለከተሜው ዜጋ ሁሉ የራሱ አሻራና ትዝታ ቢኖረውም ከወሬና አሉባልታ ጋር ተዳምሮ ግን የሆነ መሃል ላይ የሚገኝ ወይም ዥዋዥዌ ዓይነት ሊሆን እንደሚችል ገምታለሁ፡፡

መስቀልና ደቡብ ደግሞ የተለየ ታሪክና ትስስር አላቸው፡፡ መስቀል ለጉራጌ፣ መስቀል ለዳውሮ፣ መስቀል ለወላይታ፣ መስቀል ለከምባታ፣ መስቀል ለሃዲያ ወዘተ ዘመን መለወጫ ነው፡፡ አዲስ አስተሳሰብ አዲስ መንፈስ የሚጠነሰስበት፣ የአባቶች ምርቃትን ለዓመት ስንቅና ትጥቅ ለመቀበል ጉዞ ወደ ገጠርና ቀዬ የሚሆንበት፤ የወዳጅ ዘመድ ናፍቆትን ተወጥቶ የዐመት ቀለብ የሆነውን ምሥጋናና ምርቃት ተሸልመው የሚመለሱበት ወቅት ነው መስቀል፡፡ እኔም እድሜ ለመስቀል ያልኩበት ምክንያት አለኝ፡፡ ምክንያቴ ደግሞ ተጨባጭና ሀቅ ነው፡፡ ተሳትፌበታለሁ፤ ተሸልሜበታለሁ፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ ሀገሬ እውነትም የሠላም ሀገር፣ የልማት ሀገር፣ ውብና አሳቢ የሆኑ አባቶች የሞሉባት ሀገር፣ መቼም ቢሆን የማትናጋና በጽኑ መሠረት ላይ የተጣደች ሀገር መሆኗን ያረጋገጥኩበት፤ የአሉባልታና የአስረሽ ምቺው የከተማ ወሬ ደግሞ ኮሽኳሻ መሆኑን ያረጋገጥኩበት፤ እውነትም ሀገር አለኝ ስል የተኩራራሁበትን እና መንፈሣዊ ቅናት ሊንጠኝ ግድ የሆነበትን አጋጣሚ አመሰገንኩት፣ ወደድኩት፡፡

የሥራ ህይወቴን ሀ ብዬ የጀመርኩት፤ ፔሮል ላይ ፊርሜ ደሞዝ መብላት የጀመርኩት የዛሬ ዘጠኝ ዓመት ግድም በጉራጌ ዞን ነው፡፡ እንደ ዘመኔና ወጣትነቴ ግን ከተማ አፍቃሪ ነበርኩና ነው መሰለኝ አጋጣሚ የፈጠረልኝን እድል ተጠቅሜ ወደተወለድኩባት አዲስ አበባ ለመመለሰ የፈጀብኝ ሁለት ዓመት ብቻ ሆነ፡፡ የዛሬ ሰባት ዓመት አዲስ አበቤ ሆኛለሁ፡፡ የዛሬ ስብዕናዬና የሥራ ቁመናዬ ሁሉ መነሻው የጉራጌ ዞን ነው፡፡ ከጉራጌ ብዙ ተምሬያለሁ፤ ብዙ አውቄያለሁ፤ ራሴን ችያለሁ፤ ፍቅር፣ ትህትና፣ መተባበር፣ ፖለቲካ፣ ነገረ ወግና ተፈጥሮን ከአርሶ አደሩ ቀዬ ሸምቻለሁ፡፡ ያጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ እንደ ጓደኞቼ ዓመት በዓል በደረሰ ቁጥር ወደ ወላጆቼ ማምራት ግዴታዬ ነበርና ሁለት መስቀሎችን ከጉራጌ "ሚስ" አድርጌያለሁ፡፡ ትልቁን በዓል ትቼ ከግዙፉ ምርቃት ሸሽቼ ሁለቱን መስቀሎች አዲስ አበባ ላይ ማሳለፌ ቅር ቢያሰኘኝም የአስተውሎት ጉዳይ ነበርና አልቆጨኝም፡፡ ዛሬ ግን ከሰባት ዓመታት በኋላ ያለምንም ሥራ አጋጣሚ መስቀልን በጉራጌ መንደር ለማሳለፍ ጓዜን ሸክፌያለሁ፡፡ መነሻዬ አዲስ አበባ ነው። መስመሬ ደግሞ የደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ፡፡ የዞኑን ከተማ ወልቂጤ አልፌ ዋቤን ተሻግሬ በጉብሬ መገንጠያ አንዴ ፒስታውን ደግሞ የእግሯውን አስፓልት እያልኩት ነው፡፡ መድረሻዬ የምሁር አክሊሏ ሐዋርያት፣ ጨዣና እዣራ ናቸው፡፡

ጉዞው የቡድን ነው፡፡ የሓዋርያቷ አባት አቶ ሃና ትልቅ አባትና የሀገር ሽማግሌ ስለመሆናቸው ድሮም ቢሆን በዝናና ታሪክ አውቃለሁ፡፡ "ምርቃታቸው ጠብ አይልም" ሲባል በነበረኝ የሁለት ዓመታት የሥራ ላይ ቆይታ ሰምቻለሁ፡፡ ግን አይቻቸው አላውቅም፡፡ በአዲስ አበባ የሥራ ዘመኔ ግን ከጉራጌዎች ጋር በመንፈስም ሆነ በሥጋ አልተለያየንም፡፡ በአዲስ አበባ ላይ የሚደረጉ የጉራጌ ልማትና የትብብር መድረኮች ላይ ሁሉ እገኛለሁ፡፡ ይህ ግንኙነቴ የአቶ ሃናን የበኩር ልጅ እንድተዋወቀው እድል ፈጥሮልኛል፡፡ ከአቶ አየለ ሃና ጋር አሁን ከመተዋወቅም አልፈን የዝምድና ገመዳችንን በአበልጅ ቋጥረናል፡፡

የዘንድሮው የመስቀል ጉዟችንም ከአየለ ጋር እና ሌሎች ጉራጌ ካልሆኑ ጓደኞቻችን ጋር ወደ አቶ ሃና ቀዬ የተደረገ ነው፡፡ መስቀልን ለማክበር፣ ክትፎ ለመብላት፣ ንፁህ አየር ለመተንፈስ፣ ለመዝናናትና ለመታደስ ነበረ ጉዞው። ግን አጋጣሚው የአዲስ አበባን፣ የከተማውንና የዲያስፖራውን የአሉባልታ ፖለቲካ ለመታዘብ፤ ሀገሬ ካሏት ጥቂት ሟርተኞች የሚበዙ ተቆርቋሪ እና ብሄራዊ ስሜት የናጣቸው ቀና አሳቢና ሠላም አስከባሪ፣ ልማት አቀጣጣይና ቀያሽ አባቶች የተሞላች መሆኗን ለመረዳት አስችሎኛል፡፡

መስከረም 14 ቀን 2005 የምሁር አክሊል ወረዳን ከተማ ሐዋርያት ሰባት ኪሎ ሜትር አልፈን ከትንሿ መንደር ጨዛ ላይ ደርሰናል፡፡ በአቶ ሃና ቤት ለተገኘነው አየለና ጓደኞቹ ደማቅና ባህላዊ አቀባበል ተደረገልን፡፡ በጉራጌ የአሳሳም ዘይቤ አንድ ጉንጫችንን ተስመን ወደተዘጋጀልን ማረፊያ አመራን፡፡ የጉራጌ እልፍኝ ሰፊና ማራኪ ነው፤ ጅባው ወለሉን ሞልቶታል፡፡ የግድግዳው ዙሪያ በማራኪ ምንጣፎች ተለብጧል፡፡ ከሴቶች መስቀል የተራረፈውን ክትፎና አይቤ ባህላዊ በሆነው አረቄአቸው አወራርደን ሰልቅጠናል፡፡

ሌሊቱ ነጋ ማክሰኞ መስከረም 15 ቀን 2005 የእርድ ቀን ይባላል፡፡ ለመስቀል እርድ የሚውሉት ከብቶች ለጋ ሥጋ ያላቸው ጥጆች ናቸው፡፡ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ግድም በአቶ ሃና ቤት ለእርድ የቀረበውን ጥጃ ከበንና እጃችንን አጣፍተን ቆመናል፡፡ ጥጃው ታስሮ ለእርድ ዝግጁ ነው፡፡

"የመስቀልህማ ንብርሙ" /መስቀል ሁሌ እንደሚኖርና ደስታ እንዲሆን እናንተም ሁኑ/ አሉ አቶ ሃና። "አሜን" የእኛ ድርሻ ነበር፡፡ ምርቃቱ ጀመረ ማለት ነው።

"የሸዋዴንጓ ኪሳህሙ ኤቅበህ" /የከተማ ልጅ ኪሱ አይጣ/ "አሜን" ጮክ ብለን። ኪሳችን ህይወታችን ነውና፡፡ "ገኝና ሠላም ይሁን" (አገራችን ሠላም ትሁን) "አሜን" ቀጠለ ምርቃቱ፤ እኛም አሜን ብለን ስናበቃ ጉልበት ሳምን፡፡ ፍፁም ደስታ ውጦኛል፡፡ የሆነ እርባና ቢስ ነገር ከትከሻዬ ላይ ውልቅ ሲል ይሰማኛል፡፡ ሌሎቹም ጓደኞቼ የእኔ ዓይነት ስሜት ውስጥ ስለመሆናቸው ፊታቸው ያሳብቃል፡፡

እርዱ ተከናወኖ ሲያበቃ ጎረቤት፣ ወዳጅ ዘመድ ተጠራ። የቁርጥ ሰዓት ነው። የጨፍየ ሰዓት ይባላል። ከቀኑ 11 ሰዓት ቁርጡን በበርበሬ እየለወስን፣ በቅቤ እየነከርን በቅቤ በተፈላ ቡና አወራረድን፡፡ በላን ጠገብን፣ ጠጣን ረካን (በላይነ ጸገብነ ሰተይነ ወረወይነ) ከቆይታ በኋላ ወደሌላኛው ቀዬ እዥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ተጉዘን ደረስን፡፡ ወደ አቶ ሃና ወንድም ገብሬ በረዳ አፀድ፡፡ አቶ ገብሬ በረዳና ልጆቻቸው የሚኖሩት በአዲስ አበባ ሲሆን በበርካታ የኢንቨስትመንትና የልማት ሥራዎች ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ መስቀል የማይታለፍ፣ የተከበረ፣ የልማት ስንቅና ትጥቅ የሚታፈስበት ነውና አቶ ገብሬ በረዳ እነቢንያምን፣ ዳዊትና አብርሃምን እስከ ባለቤቶቻቸው ይዘው እትብታቸው በተቀበረበት ጎጆ ተገኝተዋል፡፡ ወይዘሮ አዳነችም የአቶ ገብሬ የትዳር አጋርና የመስቀሉ አቀጣጣይ ሆነው ቁርጡን ከክትፎው ጋር እየደባለቁ ከልጆቻቸው ጋር ሲመራረቁና ለሀገራችን ሠላምና ልማትን ሲመኙ ከቦታው ላይ ደረሰን፡፡

በአቶ ሃና መሪነት ቦታው ላይ ለተገኘነው እንግዶችም የፍቅር አቀባበል ተደረገ፡፡ መብልና መጠጡም በጫወታ ተዋህዶ ቀረበ፡፡ በዚህ ግቢ ከተሜው ይበዛ ነበርና የሰሞኑ የሀገሬ ፓለቲካ ለጉድ እየተወራ ነው፡፡ አሉባልታው እየተብጠለጠለ ነው፡፡ ኃላፊነት የማይሰማቸው ፕሬሶችን ጨምሮ የኒዮ ሊበራሉ ሚዲያዎች እየተወገዙ ነው፡፡ እውነታው ተገልጦ ክርክር እየተከናወነ ነው፡፡

ሰዓቱ ደረሰ፤ ክትፎው በየፈርጁ ቀረበ መራቂው አቶ ገብሬ በረዳ እና እናታቸው( እሙወች) ናቸው፡፡ "እሙወች አቡወች እድሜህነሙ ያሰንብት" /የእናቶችና አባቶችን እድሜ ያቆይልን፣ "አሜን" "የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉጉርሞ ፍቅር ይሁን" (የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በፍቅርና በመተሳሰብ ይኑር) "አሜን" የሞተም ነፍስሁታ በገነት የቶና የነምቋሚየህን (የሞተ ነፍሱን በገነት ያኑር ላለውም ረጅም እድሜ ይስጠው) ላም ህንህመሞ፣ በናህሙም፣ ወጨህሙም ይቢበነበር ልቡናያቡ (በላችሁ ጠጣችሁ፣ ተደሰታችሁ ሠላም ሆናችሁ ለማችሁ ብሎ  የሚጎረብጠው ካለ ልቦና ይስጠው) ለፀረ ልማት ኃይሎችም ልቦና ይሰጣቸው ዘንድ  ማለት ነው። ኬር የሁን ኬረ የሁን ኬር የሁን አሜን፡፡

ፍፁም ደስታ፣ ፍፁም ተነሳሽነት፣ ፍፁም ፍቅር፣ ፍፁም ተሰፋ፣ ፍፁም ኃላፊነትና አደራ ተሰማን። ፊታችን አበራ፣ ጨዋታው ቀጠለ፣ ግን የኮባ ክትፎ ሰዓት ደርሷል። ስለሆነም ወደሚጠብቁን የአቶ ሃና ቤተሰቦች አመራን። ክትፎውን በላነው ከማለት አልነው ብል ይቀለኛል፡፡

ረቡዕ መስከረም 16 ከቀኑ አምስት ሰዓት አካባቢ ደግሞ ልዩ ትዕይንት አለ። ደመራው የሚለኮስበት፣ የማሳረጊያ ምርቃት የሚከናወንበት ሰዓት፡፡ በዚህ ቦታ ደግሞ በተለየ የሚወሳው አገር ነው፡፡ ቀዬ ነው፤ ማሳ ነው፤ ልማት ነው። ቃል ኪዳንም የሚታደስበት የአዲሱን ዓመት ትጥቅ የሚታጠቁበት ነው፡፡ እነሆ እኛም የአዲሱን ዓመት የልማት ትጥቅ ታጥቀንና ሰንቀን ወደመጣንበት አዲስ አበባ የመልስ ጉዟችንን ጀመርን። በማታ ልናያቸው ያልቻልነውን የገጠር መንደሮች አሁን እየጎበኘን ነው። ማሣው ሁሉ ለምለም ነው። ቡቃያ ነው፡፡ የመስኖ፣ የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራዎች በየቀዬው ስለመከናወናቸው መስኩ ምስክር ነው፡፡ ዋናውን መንገድ የሚመግቡ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችም ደረታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ዋናው መንገድ ከአስፓልት የማይተናነስ እና የማይጎረባብጥ የጠጠር መንገድ ነው። በእነዚህ መንደሮች በእርግጥም በርካታ የልማት ሠራዊቶች ፈርተዋል፤ የኅብረተሰብ ተሳትፎ የለት ቀለብና የውዴታ ግዴታ ነው፡፡ ለመስቀል የሚገባው ከተሜ ደግሞ እርሾው ላይ ጠብ ሳያደርግ አይመለስም። በከተማም ሆኖ ልማታዊ እጁ ረዥም ነው፡፡ ኬር ይሁን አሜን፡፡

-